Haile Selassie I - Harar Military Academy North America
ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሐረር ጦር አካዳሚ ሰሜን አሜሪካ

# HMAHAA Members November 23, 2025 Bi-monthly Meeting Highlights

የቀዳማዊ ሐይለስላሴ/ሐረር ጦር አካዳሚ ምሩቃን ማህበር በሰሜን አሜሪካ በሁለት ወር አንድ ጊዜ እየተሰበሰበ አባላትንና ቤተሶቦቻቸውን የሚያገናኘው ስብሰባ ህዳር 23 ቀን (November 23, 2025) በተለመደው ስፍራ ተካሂዷል። ይህ መደበኛ ስብስባ አባላትና ቤተሰቦቻቸው ተገናኝተው እርስ በእርስ እንዲጠያየቁ፤ የምሳና የግል ጨዋታ ጊዜ እንዲኖራቸው፤ በአንዳንድ ማህበራዊ ነክ ጉዳዮች ላይ ውይይትና ምክክር በማድረግ እርስ በእርስ የሚረዳዱበትን ሁኔታዎች ለማመቻቸት ታልሞ የሚዘጋጅ ነው። በተጨማሪም ማህበሩ አባላት በግል ለሚያጋጥማቸው አንዳንድ ማህበራዊ ችግሮች መጠነኛ እርዳታዎችን በመስጠት አባላትን ይረዳል። በየሁለት ወሩ የሚካሄደው ይህ ስብሰባ የሚስተናገደው በአባላት በጎ ፈቃድ ሲሆን በማህበሩ ደንብ መሰረት ቅደም ተከተል ወጥቶ ተረኛ አስተናጋጅ ምሳና ሌሎች የመስተንግዶ ወጪዎችን ችሎ በግሉ ስብሰባውን ያዘጋጃል።



ማህበሩ በዓመት ውስጥ ስድስት ስብሰባዎችን የሚያካሂድ ሲሆን በጃኑዋሪ ወር ተጀምሮ በህዳር ወር የሚደረገው ስብስባ የዓመቱ መጨረሻ ስብሰባ ነው። የ2025 ዓ.ም የመጨረሻ ስብሰባ የተካሄደው ኖቬምበር 23 ቀን (November 23, 2025) ነበር። ስብሰባውን አዘጋጅተው ያስተናገዱት ኮሎኔል ጎሹ ወልዴና ባለቤታቸው ወይዘሮ ማርታ አበበ ከልጆቻቸው ጋር በመሆን ነበር። በእለቱ ***35*** አባላትና ***21*** የቤተሰብ አባላት፤ በድምሩ ሃምሳ ስድስት ***(56)*** አባላት ተገኝተዋል። ከምሳ በፊት የማህበሩ ስራ አመራር ኮሚቴ ሁለት ሶስተኛው (2/3ኛው) የማህበሩ አባላት መገኘታቸውን ካረጋገጠና "የእንኩዋን ደህና መጣችሁ" ሰላምታ ካቀረበ በኋላ በቅርቡ ከዚህ ዓለም በሞት ለተለዩት የአካዳሚው ምሩቅና የ16ኛ ኮርስ አባል መ/አለቃ ዳምጤ ይልማ የአንድ ደቂቃ የሂሊና ጸሎት ተደርጎላቸዋል።





ከ***2፡00-3፡00*** ፒ.ኤም በነበረ ጊዜ  አባላት የምሳና የግል ጨዎታ  ጊዜ ነበራቸው። በኮሎኔል ጎሹ ወልዴና በወይዘሮ ማርታ አበበ የተዘጋጀው የምሳ ፕሮግራም ከተጠናቀቀ በኋላ ያልታሰበ ድንገተኛ ("Surprise")  "ምስጋና ሰርቲፍኬት" ለኮሎኔል ጎሹ ወልዴ ተበርክቶላቸዋል። ኮሎኔል ጎሹ ወልዴ የኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣን ሆነው ባገለገሉበት ወቅት ለሰሩት በጎ ተግባር ከቀድሞ አርሲ አስተዳደር ክልል ሁሩታ ወረዳ ማህበረሰብ የተላከላቸው "የምስጋና ደብዳቤና የእውቅና ሰርቲፊኬት" የወረዳው ማህበረሰብ ወክሎ በላካቸው አባላት አማካይነት ተበርክቶላቸዋል። ኮሎኔል ጎሹ የኢትዮጵያ ትምህርት ምንስትር ሆነው ባገለገሉበት ወቅት ለስራ ጉብኝት ወደ ሁሩታ ወረዳ በሄዱበት አንድ አጋጣሚ የአከባቢው ሕዝብ በሁሩታ ወረዳ ውስጥ 2ኛ ደረጃ

ት/ቤት ስላልነበረ ልጆቻቸውን ሩቅ ስፍራ ልከው ማስተማር እንዳልቻሉ በመግለጽ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት እንዲከፈትላቸው አቤቱታቸውን ለኮሎኔል ጎሹ ያቀርባሉ። ወዲያው አዎንታዊ መልስ ለመስጠት ለኮሎኔል ጎሹ ጥያቄያቸው ድንገተኛ ቢሆንም አቤቱታቸውን በጽሞና ካዳመጡ በኋላ ጥያቄቸውን ለብቻቸው መወሰን እንደ ማይችሉ ገልጸው፤ ነገር ግን ከስራ ባልደረቦቻቸው ጋር ተነጋግረው መልስ መስጠት ይችሉ ዘንድ ተወካዮች መርጠው እንዲልኩ ቃል ገብተው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ።

ይህ ውሳኔ በተሰጠ አንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ከወረዳው የተመረጡ የሕዝብ ተወካዮች አዲስ አበባ ሄደው አቤቱታቸውን ለትምህርት ምንስትሩ አቀረቡ። ኮሎኔል ጎሹ ከስራ ባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን ተወካዮቹን ተቀብለው ካነጋገሩ በኋላ የተጠየቀው 2ኛ ደረጃ ት/ቤት እንዲከፈት ፈቀዱላቸው። የት/ቤቱ ስራም በአስቿካይ ተጠናቅቆ ትምህርት እንዲጀመረ መመሪያ ሰጥተው ተወካዮቹን ወደ መጡበት ሸኝቷቸው ነበር። ተወካዮቹ ከተመለሱ በኋላ የት/ቤቱ ስራ በ1974 ዓ.ም ተጀምሮ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጠናቅቆ በመከፈቱ የወረዳው ህብረተሰብ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቱ ተጠቃሚ ለመሆን ችሏል። ታዲያ ይህንን ታላቅ በጎ ተግባር የፈጸሙትን ባለውለታ ኮሎኔል ጎሹ ወልዴን የወረዳው ማህበረሰብ ሁልጊዜም ሲያስታውሷቸው እንደ ሚኖር ተወካዮቹ በደብዳቤያቸው ገልጸዋል።

በመሆኑም የህብረተሰቡን ድምጽ ሰምተው አፋጣኝ ምላሽ በመስጠት በጎ ተግባር ለፈጸሙት ለእኝህ የህዝብና የአገር ባለውለታ ሰው ከአከባቢው ህብረተሰብ የተላከላቸው “የምስጋና ደብዳቤና የእውቅና ሰርቲፍኬት” ህዳር 23 ቀን 2025 በተካሄደው የአሉምናይ ማህበራችን ስብሰባ ላይ በተወካዮቻቸው አማካይነት ለኮሎኔል ጎሹ ወልዴ ተበርክቶላቸዋል። ከማህበረሰቡ የተላከው የምስጋና ደብዳቤ በሻለቃ ንጉሴ ሞጎስ በንባብ ከተሰማ በኋላ በስማቸው የተዘጋጀው የምስጋና ሰርቲኬት በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው አማካይነት እንዲሰጣቸው ተወካዮቹ የጠየቁ ቢሆንም በእድሜና በማእረግ ቀደምት የሆኑት የጦር አካዳሚ አንደኛ ኮርስ ምሩቅና የአሉምናይ ማህበራችን አባል ብ/ጄኔራል መኮንን ገብረማርያም ሽልማቱን እንዲሰጡ ተደርጓል። የአሉምናይ ማህበሩ አባላትም ምስጋናቸውንና አድናቆታቸውን በጭብጨባ ገልጸዋል።

ከ***3፡00-5፡00*** ፒ.ኤም በነበረ ጊዜ አባላት በቀረበው አጀንዳ ላይ ተወያይተው ውሳኔ አስተላልፈዋል። ለውይይት የቀረበው አጀንዳ "ቀዳማዊ ሃይለስላሴ/ሐረር ጦር አካዳሚ ምሩቃን አሉምናይ ማህበር" ከተመሰረተ በ2026 ዓ.ም 25ኛ ዓመቱን ስለ ሚያስቆጥር "የምስረታው 25ኛ ዓመት በተለየ ሁኔታ ይከበር ወይስ በመደበኛ ስብሰባ ቀን በአነስተኛ ዝግጅት ታስቦ ይዋል?" የሚሉ ሁለት ሃሳቦች ለውይይት ቀርበው ነበር። የማህበሩ አባላት በሁለቱም አማራጮች በሰፊው ከተወያዩ በኋላ በድምጽ ብልጫ እንዲወሰን በአሳሰቡት መሰረት አባላት ድምጻቸውን ሰጥተው "ከ2/3ኛ አባላት በላይ በልዩ ሁኔታ ይከበር" የሚለውን ሃሳብ ስለደገፉ በአብላጫ ድምጽ በዓሉ በልዩ ሁኔታ እንዲከበር ተወስኗል። በዓሉ በልዩ ሁኔታ ይከበር የሚለው ሃሳብ በድምጽ ብልጫ አሸናፊ ከሆነ በኋላ "የበዓሉ አዘጋጅ ኮሚቴ" እንዲመረጥ በተወሰነው ውሳኔ መሰረትም የአዘጋጅ ኮሚቴ ጥቆማ ተደርጎ የሚከተሉት ስምንት አባላት በአዘጋጅ ኮሚቴነት ተመርጠዋል።

1. ኮሎኔል ገበየሁ ኦስማን
2. ሌ/ኮሎኔል ካሱ ታዬ
3. ሻለቃ ሸዋረጋ ጸጋዬ
4. ሻለቃ ንጉሴ ሞገስ
5. መ/አለቃ ዮናስ አለማየሁ
6. ወይዘሮ ሙሉብርሃን ተፈራ
7. አቶ አንተነህ ንጉሱ
8. እ/መ ብርሃኔ ወ/ሚካኤል

የተመረጡት አዘጋጅ ኮሚቴ አባላት የራሳቸውን ሰብሳቢና ጸሐፊ መርጠው በማሳወቅ ስራቸውን እንዲጀምሩ ውሳኔ ተሰጥቶ አጀንዳው ተጠናቋል።

በመጨረሻም የአሉምናይ ማህበሩን መስተንግዶ በአስደሳች ሁኔታ ላዘጋጁትና ላስተናገዱት ኮሎኔል ጎሹ ወልዴና ወይዘሮ ማርታ አበበ እንዲሁም ለመላው ቤተሰባቸው ምስጋና ቀርቦ የእለቱ ስብሰባ በ***5፡00*** ፒ.ኤም ተጠናቋል። የሚቀጥለው የአሉምናይ ማህበር ስብሰባ አስተናጋጅ ሻለቃ ሃይለማርያም አባይና ወይዘሮ ትሰሚ ሃይሌ መሆናቸውም ለአባላት ተገልጿል።

የአሉምናይ ማህበሩን ስብሰባ ተሳታፊዎች በከፊል የሚያሳዩ ፎቶግራፎች




EXIT




COMMUNITY CENTER